# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ሐምሌ 21 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ሙስሊሙ በገፍ እየታፈሰ ወደ ሰንዳፋ ተጋዘ፤**

**የወያኔ ባለስልጣናት መሀከል ቡድንተኝነቱ አይሎዋል፤**

**መከላከያ ውስጥም እየተዛመተ ነው ተባለ፤**

**ፍትህ ጋዜጣ እንዳይታተም በረከት ስምኦን ትዕዛዝ መስጠቱ ተጋለጠ፤**

የወያኔን ቡድን ተቃውመዋል የተባሉ የሙስሊሙ አማኞችን ሲያስተባብሩ ነበር የተባሉት የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች ከያሉበት እየተለቀሙ ለእስር እየተዳረጉ ባለበት በዚህ ወቅት በድጋሚ ዓርብ ሐምሌ 20 ቀን 2004 ዓ.ም በአንዋር መስጊድ ታላቅ ተቃውሞ መስተጋባቱ በወያኔ ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤ መፍጠሩ ታወቀ::

ሙስሊሙ ህዝብ ሐምሌ 14 ቀን 2004 ዓ.ም መርካቶ አንዋር መስጊድ ውስጥ እና ውጭ ተቃውሞ በማሰማቱ ብቻ የወያኔ የፀጥታ ኃይሎች ያከሄዱትን ዘግናኝ ጭፍጨፋ ድብደባና እንግልት የተለያዩ ወገኖች እያወገዙት ይገኛሉ:: ከዚህ በተጨማሪ የወያኔ ቡድን ሙስሊሙን ሕዝብ የሽብርተኛነት ቅፅል እየሰጠ ለማስፈራራት ጥረት ቢያደርግም በድጋሚ ዓርብ ዕለት በሙቶ ሺህ የሚቆጠረው ሙስሊም በታላቁ አንዋር መስጊድ ተቃውሞ ማሰማቱ ወያኔን ግራ እንዳጋባው ለማወቅ ተችሎዋል::

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ ሐምሌ 14 ቀን 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ በተከሰተው ብጥብጥ ከተማዋ በተኩስ ስትናጥ የዋለች ሲሆን ከተቃውሞ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውን ሁሉ

አፍሶ ለእስር መዳረጋቸውና ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ደግሞ በጥይት ተመትተው ሆስፒታል መግባታቸው ታውቆዋል።

በዕለቱ በተከሰተው ብጥብጥ የአንበሳ አውቶቡስን ጨምሮ ሌሎች መኪኖች በድንጋይ የተሰባበሩ ከመሆኑም በላይ የተወሰኑ ሱቆችም የተቃውሞው ተሳታፊ በመሆን ተዘግተው መሰንበታቸውንም ይሄው የደረሰን የጥቆማ አጋልጦዋል።

በሙስሊሙ ወገናችን ላይ ጥቃት ያደረሰት ስናይፐር መሳሪያ የታጠቁ የፌዴራል ፖሊስ እና የአግአዚ ጦር አባላት ሲሆኑ ከአሜሪካ በእርዳታ የተሰጡት ሀመር የጦር ሜዳ መኪኖችም በዚሁ ተግባር ተሳታፊ እንደነበሩም ከአይን እማኞች የደረሰን ጥቆማ ይገልፃል። ህዝበ ሙስሊሙም የተከፈተበትን ተኩስ ሳይፈራ በድንጋይ የሞት ሽረት ትግሉን ከፖሊስ ጋር ሲያደርግ እንደዋለም ለማረጋገጥ ተችሎዋል። በተለይ በአንዋር እና በቤኒን መስጊዶች የተነሳው ተቃውሞና ብጥብጥ እጅግ አስፈሪ የነበረ በመሆኑ የአግአዚ ጦር አባላት መትረየስ በተደቀነባቸው ሀመር መኪኖች በስፍራው ደርሰው የተኩስ እሩምታ መክፈታቸውን የአይን እማኞቹ ገለፃ አስረድቶዋል።

የሙስሊሙን መብት ያስከብራሉ ተብለው በህዝቡ የተመረጡት የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች በተኩሱ መሀከል እጃቸውን ከፍ አድርገው ወደ ላይ በማውጣት አላህ ወአክበር! እያሉ ህዝበ ሙስሊሙ ከጥቃቱ እንዲያመልጥ ከፍተኛ ልመናደጋግመው ሲያሰሙ የነበረ ሲሆን ይህን ማለታቸው ቅስቀሳ እያደረጉ ነው በሚል ከያዟቸው በኋላ በዱላና በሰደፍ እየቀጠቀጡዋቸው ወዳልታወቀ ስፍራም እንደወሰዱዋቸው በቦታው ላይ ከነበሩ የአይን እማኞች ለማወቅ ተችሏል።

በተቃውሞው ላይ የጎላ እንቅስቃሴ አድርገዋል ተብለው በስም ዝርዝር የተለቀሙትን የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባትን ጨምሮ ሌሎች የሙስሊሙን የመብት ጥያቄ ያነሱትን ሁሉ የወያኔ ቡድን ከያሉበት በቀንና በሌት በውድቅት...... እያፈሰ በተለያዩ እስር ቤት ውስጥ ያጎራቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሎዋል።

በተለይ የሙስሊሙ መፍትሔ አፈላላጊ የተባሉት በሙሉ ከያሉበት ተይዘው በተለያዩ እስር ቤቶች ውስጥ የታሰሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ይህ ቀረሽ የማይባል ዘግናኝ ድብደባና እንግልት የደረሰባቸው መሆኑን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ከቤተሰቦቻቸው ያገኘውን መረጃ ዋቢ በማድረግ ገልጾዋል።

ቅዳሜ እለት ሐምሌ 14 ቀን 2004 ዓ.ም በተከሰተው ብጥብጥ እና ሁከት ታፍሰው የተያዙ ሙስሊሞች ከ15 አውቶቡስ በላይ ተጭነው ሰንዳፋ ፖሊስ ኮሌጅ የታሰሩ ሲሆን በዚህ ግቢ ውስጥ ለማሰቃየት እና አንቆ ለመግደል በሰለጠኑ ፖሊሶች አማካኝነት ጠዋት ጠዋት በቀዝቃዛ ውሀ በተሞላ በርሜል ውስጥ እንዲዘፈዘፉ ከዚያም ወጥተው በባዶ እግራቸው በአሸዋ ላይ ለረዥም ሰዓት እንዲሮጡ እየተደረጉ መሆኑን ይኸው የቤተሰቦቻቸው ጥቆማ አስረድቶዋል።

የሙስሊሙ ተወካይ የሆኑ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች በሙሉ ለእስር የተዳረጉ ሲሆን ዶ/ር ከሚል ገለቱ፤ጀማል ያሲን፤ሱልጣን አማን፤ኑሩ ቱርጂ ፤ሰኢድ እና የኮሚቴው ቃል አቀባይ የሆነው አህመዲን ጀበል ክፉኛ የተደበደቡ መሆናቸው ታውቋል።

ከሽብርተኞች ጋር ግንኙነት አላቸው የሚል ሀሰተኛ ውንጀላ እያቀረበ ባለበት በዚህ ግዜ ከወረዳ አስተዳዳሪ እስከ ሚኒስቲር ድረስ አንዳንድ የወያኔ ባለስልጣናት በሙስሊሙ ላይ እየተወሰደ ያለው አላስፈላጊ እርምጃ ከመሆኑም በላይ ለወደፊቱ ዛላቂ መፍትሔ አያመጣም በማለት በይፋ እየተቃወሙ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሎዋል::

የወያኔው የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነሩ ወርቅነህ ገበየሁ አለቆቹ ውስጥ ውስጡን እርስ በርስ በሙስሊሙ ጥያቄ እየተወዛገቡና ቃላት ጭምር እየተመላለሱ ባለበት በአሁኑ ሰዓት በታሰሩት የሙስሊሙ አማኞች ላይ በቅርቡ ክስ ተመስርቶ አስፈላጊው ቅጣት ይወሰንባቸዋል በማለት መግለጫ ሰጥቷል:: ይህ መግለጫ ከተሰጠ በኋላ ሙስሊሙ በአንዋር መስጊድ አስገራሚ ተቃውሞ ማሰማቱ ለወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ትልቅ የራስ ምታት እንደሆነ ተጠቁሞዋል::

የፖሊስ ኮሚሽነሩ ከአንዴም ሶስት አራት ጊዜ ከወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ለውይይት ቀርበው የነበሩትን የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎቹን ፍቃድ የሌላቸው ህገ ወጥ ሽብርተኞች እያለ እያጣጣለ መግለጫ በሰጠ በማግስቱ ሐምሌ 20 ቀን 2004 ዓ.ም ስድስት ሰዓት ላይ ሙስሊሙ በአንዋር መስጊድ ግቢ እና ዙሪያው በመገኘት በዝምታ ፤እጃቸውን በማመሳቀልና እንዲሁም በጭብጨባ በማስተጋባት ተቃውሞ ያቀረቡ ሲሆን በተለይ ለረዥም ሰዓት መሪዎቻችን ይፈቱ በማለት በመቀመጥ ብቻ ያሰሙት ተቃውሞ አስገራሚና የሌሎቹንም እይታ የሳበ እንደነበር ለማወቅ ተችሎዋል::

ከሙስሊሙ ህዝብ ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ አምስት የሳዑዲ ዜግነት ያላቸው ሰዎች ያለ ኤምባሲያቸው እውቅና በደህንነት ተይዘው በአስቸኩዋይ ከሀገር እንዲወጡ መደረጉም ታውቆዋል::

እነዚህ የሳዑዲ ዜጎች በትርምስ ስራ እጃቸው አለበት በሚል ከያሉበት በድንገት ተይዘው ወደ ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተወስደው እቃዎቻቸውን ሳይዙ ባዶ እጃቸውን ምሽቱን ከሀገር እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን ዜጎቻችን ከሀገር ሲወሰዱ ኤምባሲያችን ሊያውቅ ይገባል በሚል የሳኡዲ መንግስት ቅሬታ ያቀረበ መሆኑ ይሰማል::

በእንዲህ እንዳለ የወያኔ ከፍተኛ የሙስሊም ባለስልጣናት በክልል ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ሳይገኙ በመቅረታቸው በአባላቱ መሀከል ችግር መኖሩን ይጠቁማል በሚል ታዛቢዎች ግምታቸውን ይሰጣሉ::

በአዳማ (ናዝሬት) ከተማ በኦሮሚያ ምክር ቤት በተደረገው የዓመታዊ መዝጊያ ስብሰባ ላይ ከዚህ በፊት ቀርተው የማያውቁ ሙስሊም ባለስልጣናት በአሁኑ ስብሰባ ላይ ሳይገኙ መቅረታቸው ታውቆዋል::

በተመሳሳይ ደኢህዴንም በአዋሳ ከተማ ባደረገው ዓመታዊ መዝጊያ ስብሰባ ላይ እነ ሬድዋን ሁሴን ይገኛሉ ተብሎ ተጠብቆ የነበረ ሲሆን ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ሳይገኝ በመቅረቱ በወያኔ ውስጥ ክፍፍሉን አጉልቶ የሚያሳይ ሳይሆን አይቀርም ግምት አለ::

ባለፈው ሳምንት የወያኔ ቡድን ከፍተኛ ባለስልጣን የሆነው ጁኔዲ ሰዶ ባለቤት ወ/ሮ ሀቢባ ከሣዑዲ አረቢያ ኤምባሲ ውስጥ ገንዘብ እና በዓረብኛ የተፃፈ የሚበተን ወረቀት ይዛ ስትወጣ

በደህንነቶች እጅ ከፍንጅ የተያዘች ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ጁኔዲን እና ሌሎች መሰል ባለስልጣናት በተቃውሞው እጃቸው እንዳለበት አመላካች ነው ተብሎዋል፡፡

ወ/ሮ ሀቢባ በዕለቱ በሳዑዲ ኤምባሲ በር ላይ በደህንነት ቁጥጥር ስር በዋለችበት ወቅት ቀጥታ ወደ መዕከላዊ ምርመራ የተወሰደች ሲሆን ባለቤትዋ ጁኔዲም ደግሞ ለጥያቄ ትፈለጋለህ ተብሎ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ሀሰን ሽፋ ቢሮ ተጠርቶ ለሰዓታት ከቆየ በሁዋላ ከእስር ቢለቀቅም ከዛን ዕለት ጀምሮ በስውር ደህንነት ልዩ ክትትል እየተደረገበት መሆኑም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ከ10 ዓመት በፊት የአወሊያ ትምህርት ቤት መምህርና የተቃውሞ ሰልፍ አስተባባሪ የነበረው ሬድዋን ሁሴን መለስ በአጭር ግዜ የደቡቡ ባለስልጣንና የመለስ ዋነኛ አማካሪ በማድረግ የሾመው መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን  ዛሬ መለስ የአልጋ ቁራኛ በሆነበት ጊዜ የዙፋኑ አስጠባቂ ከመሆን ይልቅ ከዳው እየተባለ በሰፊው መነጋገሪያ መሆኑም እየተገለጸ ነው፡፡

ሬድዋን ሁሴን ከሙስለሙ ተቃውሞ ጀርባ እጁ ሳይኖርበት አይቀርም በሚል በልዩ ደህንነት ጥበቃ እየተደረገበት ነው ያሉት ምንጮቹ ሰሞኑን የደቡብ ክልል ዓመታዊ በጀት ለማጽደቅ በአዋሳ በተደረገው ዝግጅት ላይ አለመገኘቱን ገልፀዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሚሰሩና በየዞንና ወረዳ ውስጥ የተመደቡ ሙስሊም ባለስልጣናት ጭምር በስውር እየታሰሩ እንደሚገኙ ዘገባ የደረሰን ሲሆን ይህ ዜና እስከ ተጠናቀረበት ድረስ አፈሳው እንዳላቆመና ይብሱን ተስፋፍቶ መቀጠሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ ዜና በአሁኑ ሰዓት በወያኔ ቡድን ውስጥ መከፋፈሉ መኖሩ በሰፊው እየተነገረ ሲሆን ይህ ክፍፍል  ወደ መከላከያው ውስጥም እንዳይዛመት በመስጋት መጠነኛ ለውጥ መደረጉን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ፡፡

እስከ ዛሬ የሰላም አስከባሪው መምሪያ ኃላፊ ተብሎ ሲቀርብ የነበረው የህወሀቱ ጄኔራል ቀርቶ የብአዴኑ ሐሰን መሐመድ በቦታው መቀመጡን ጠቅሰው  የምስራቅ እዝ ምክትል አዛዥ አድርገው የኦህዴዱን ብ/ጄ/ል ጉዲና ጌታቸው የተባለውን ማስቀመጣቸውን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

ይህ የሆነው ሰሞኑን የህወሀት ጄኔራሎች ብቻ ስብሰባ በመቀመጣቸው የተበሳጩ የወያኔ ባለስልጣናት ባነሱት ጥያቄ ዙሪያ መልስ ለመስጠት ሳይሆን አይቀርም ያሉት ምንጮቹ በተለይ መለስ ታምሞ ከሀገር ከወጣ በሁዋላ በመከላከያም ውስጥ የጠራ አቋዋም እንደማይታይ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም በማስተዋል የህትመት እና ማስታወቂያ ስር የሚታተመው ሳምንታዊ ፍትህ ጋዜጣ ከእንግዲህ ለገበያ እንደማይቀርብ የብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት አለቆች የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በመጥቀስ ገለፁ፡፡

ዘወትር ዓርብ ለንባብ የሚቀርበው ይሄው ጋዜጣ በወያኔ ቡድን ላይ የሰላ ትችት ከማቅረቡም በላይ የታመኑ መረጃዎችን አፈላልጎ በማውጣት ለህዝቡ ሲያቀርብ የነበረ ሲሆን ባለፈው ሳምንት በመለስ ዜናዊ ህመም እና ከህመሙ በሁዋላ ያሉ ጉዳዮችን በሰፊው በመዳሰሱ ከ80 ሺህ ብር በላይ ወጪ ተከፍሎ የታተመው 30 ሺህ ቅጂ በማተሚያ ቤቱ መጋዘን ውስጥ እንዲቆለፍበት መደረጉ ታውቆዋል።

ለጋዜጣው አዘጋጆች የሐምሌ 13 እትሙን በመጋዘን እንዲገባ ያስደረገው ፍትህ ሚኒስትር ነው ተብሎ ተነግሮዋቸው የነበረ ቢሆንም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ግን በረከት ስምኦን በምስጢራዊ ትዕዛዝ የፈፀመው መሆኑን የብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ምንጮች አጋልጠዋል።

በአሁኑ ሰዓት ከ20 ዓመት በላይ የብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ስራ አስኪያጅነት ተቀምጣ ያለችው ሙሉብርሀን የተሰኘችው የህወሀት ሰው ከበረከት በተሰጣት ጥብቅ ትዕዛዝ መሰረት ከእንግዲህ በማተሚያ ቤቱ ፍትህ ጋዜጣ እንደማይታተም በይፋ መግለጽዋንም ምንጮቹ አስረድተዋል።